ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies (FSS)

ነሐሴ 2002 ዓ.ም. **የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች** ቁጥር 24

# የችጋር ኑሮና የዕርዳታ ሚና በሰሜን ወሎ

የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው፡፡

የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል፡፡

በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በአዋሳ (በ100.9 ሞገድ) ከተሞች ኤፍ.ኤም.ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል፡፡

በድረ-ገጹ የሕትመት ውጤቶቹን ዝርዝር ያቀርባል፡፡

በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን፡፡

## 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ - በተለይም ሰሜን ወሎ - በ1966 እና በ1977 ዓ.ም በተከሰተው አስከፊ ድርቅና ረሀብ ምክንያት የዓለምን ትኩረት አግኝታ ነበር፡፡ ከ1977ቱ ረሀብ በኋላ በተወሰዱት የረሀብ አደጋን የመከላከልና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መርሐ ግብር እርምጃዎች ምክንያት እንደቀድሞዎቹ ያለ አስከፊ የምግብ እጦት አደጋ ባይከሰትም ለበርካታ የሰሜን ወሎ ኗሪዎች ስር የሰደደ የምግብ እጦት የእለት ከእለት የኑሮ ገጽታ መሆኑ አልቀረም፡፡

በየጊዜው ለሚከሰተው የምግብ ዋስትና እጦት መንስኤዎቹ ግብርናው በዋናነት በዝናብ ውሃ ላይ ጥገኛ መሆኑ፣ ፈጣን የህዝብ ቁጥር እድገት፣ የእርሻ መሬት ጥበት፣ ምርታማ ያልሆኑ የግብርና ዘዴዎች በስፋት ጥቅም ላይ መዋል፣ የአፈር መሸርሸር እና የዝናብ መጠንና ስርጭት መዛባት ናቸው፡፡ በተጨማሪም እርሻ ነክ ያልሆኑ ሙያዎች ላይ የሚደረገው ባህላዊ ተጽእኖ፣ የጥቃቅን ኢንዱስትሪዎችና ንግድ አለመዳበር እና ህብረተሰቡ ኑሮውን ለማሸነፍ የሚሰማራባቸው የሙያ ዘርፎች ውስንነት ችግሩን አባብሰዉታል፡፡ የአየር ጠባይ ለውጥ ደግሞ ከላይ በተዘረዘሩት ስር የሰደዱ ምክንያቶች የሚከሰትን የምግብ እጥረት ችግር በእጅጉ ያባብሳል፡፡ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ኑሮአቸው ከዝናብ መኖርና አለመኖር ጋር የተቆራኘ በመሆኑ የከባቢ አየር ለውጥ ቀጥተኛ ተጠቂዎች እንደሚሆኑ ግልጽ ነው፡፡

የዚህ ጽሁፍ ዓላማ ኢትዮ-ዴንማርክ ጥምር የልማት ፕሮግራም በአማራ ክልል (ሰሜን ወሎ) ለድንገተኛ የእህል እጥረት ከሚሰጠው ድጋፍ በተጨማሪ በግብርና፣ በጤናና በትምህርት ዘርፎች ያከናወነው ሁለ-ገብ የልማት ስራ ስኬታማነት ለመፈተሽ የተደረገውን ጥናት ውጤት በአጭሩ ማቅረብ ነው፡፡ የፕግራሙ ዋና ግብ በቆቦና በሀብሩ የሚገኙ ሃያ ሶስት የተመረጡ ቀበሌዎች የተሻለ የምግብ ዋስትና እንዲኖራቸው ማድረግ ነበር፡፡ ጥምር የልማት ፕግራሙን የፈጠሩት በርካታ በኢትዮጵያና በዴንማርክ የሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሲሆኑ እነሱም የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኀበር፣ የዴንማርክ ቀይ መስቀል ማኀበር፣ ሉትራን የዓለም ፌዴሬሽን/የኢትዮ-ኢቫንጀሊካል መካነ- ኢየሱስ ቤተክርስቲያን፣ የዴንማርክ ቤተክርስቲያን እና የዴንማርክ ሕጻናት አድን ድርጅት ናቸው፡፡ እነዚህ ድርጅቶች በተለያዩ ዘርፎች ተሳትፈዋል፡፡ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀልና የዴንማርክ ቀይ መስቀል በጤናው ዘርፍ የተቀረጹ ፕሮጀክቶችን በመተግበር ተሳትፈዋል፤ ሉትራንና የዴንማርክ ቤተክርስቲያን ተራድኦ ድርጅት በግብርናና በማህበራዊ ልማት ዘርፎች ሲሳተፉ የዴንማርክ ህጻናት አድን ደግሞ የትምህርትና የህጻናት መብት ፕሮጀክቶችን በማቀናጀት ድርሻውን አበርክቷል፡፡ ጥምር ፕሮግራሙ በስራ ላይ የቆየው ከ1990 ዓ.ም እስከ 2001 ዓ.ም ነው፡፡

## 2. የጥናቱ ዘዴዎችና አካባቢው

የጥምር ፕሮግራሙ በሚተገብራቸው ፕሮጀክቶች ምክንያት በህብረተሰቡ ዘንድ የሚታዩ ለውጦችን የሚገመግምበት የምርምር አካል ነበረው፡፡ የዚህ አካል ዋና ዓላማ የታዩ ለውጦችን በዝርዝር መመርመርና በአካባቢው የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና የህዝቡን አቅም ለመገንባት የድንገተኛ እርዳታና የልማት ስራዎች እንዴት በቅንጅት ሊሰሩ እንደሚችሉ ማጥናት ነበር፡፡ ለጥናቱ መረጃ ለመሰብሰብ አሃዛዊ (quantitative) እና የህዝብ አስተያየቶችን በማውጣጣት ገላጭ (qualitative) ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በሁለቱም ዘዴዎች በቤተሰቦች ላይ በተደረገው ጥናት በተመረጡ ቤተሰቦች ላይ ብቻ አትኩሮ እንዲዘልቅ መደረጉ ዓይነተኛ ባህሪው ነበር፡፡ ይህም በአንጻራዊነት ብዙ ሊባል በሚችል የጥናት ናሙና (በጠቅላላው 160 ቤተሰቦች) ላይ የረጅም ጊዜ ክትትል ለማድረግና የህዝቡን አኗኗርና የችግር አፈታት ብልሃቶች ለማወቅ ያስቻለ ልዩ አጋጣሚ ፈጥሯል፡፡ ጥናቱ ባጠቃላይ ከሁለቱ ወረዳዎች (ከቆቦና ከሀብሩ) በተወሰዱ ስምንት ቀበሌዎች ላይ ያተኮረ ነበር፡፡

## 3. የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች

የጥምር ፕሮግራሙ የጥናት አካል የደረሰበት አጠቃላይ ድምዳሜ ከ1991 ዓ.ም እስከ 2000 ዓ.ም በአካባቢው ህዝብ የምግብ ዋስትና ላይ በግልጽ የሚታይ መሻሻል እንደነበረ ነው፡፡ ይህንን ለማሳየት ከሚረዱ ጠቋሚዎች አንዱ እያንዳንዱ ቤተሰብ ያለው የንብረት ዓይነትና ብዛት ነው (የቤት ቁሳቁስ፣ ጌጣጌጥ፣ ከብቶች፣ የእርሻ መሳሪያዎች)፡፡ ይህ በተለይ ለድንገተኛ የምግብ እጥረት የተጋለጡ አካባቢዎች ላይ ዓይነተኛ ጠቋሚ ነው፡፡ በዚህ ረገድ አዎንታዊ ለውጥ ታይቷል፡፡ አበረታች መሻሻል የታየባቸው ሌሎች ጠቋሚ ነገሮች የእህል ክምችት (ጥራጥሬና የቅባት እህሎች) እና አመጋገብ (በቀን ሶስት ጊዜ የሚበሉ የቤተሰብ አባላት ቁጥር) ናቸው፡፡ በተጨማሪም በፕሮግራሙ ዘመን የአካባቢው ህብረተሰብ ለምግብም ሆነ ለሌሎች ጉዳዮች (ለልብስ፣ ለቤት ቁሳቁስ፣ ወዘተ) የሚያወጣው ወጪ ጨምሯል፤ ይህም ገቢ መጨመሩን ያመለክታል፡፡ ለምሳሌ ለልብስ የተደረገው ወጪ በሶስት እጥፍ ጨምሯል፡፡ በትምህርት ላይ የተደረገው ወጪ ደግሞ በሰባት እጥፍ አድጓል፡፡ ይህም ጥምር ፕሮግራሙ

በተንቀሳቀሰባቸው አካባቢዎች የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ምን ያህል እንደተስፋፋ ያሳያል። ከ1991 ዓ.ም እስከ 2000 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ጥናቱ ባካተታቸው ቤተሰቦች የሚገኙና የአንደኛ ደረጃ ትምህርቸውን የሚከታተሉ ህጻናት ቁጥር በሶስት እጥፍ አድጓል። የቤተሰብ ምጣኔም በአዎንታዊ መልኩ ለውጥ አምጥቷል፤ ጥናቱ ባካተታቸው ቤተሰቦች ውስጥ በተመሳሳይ ጊዜ የውልደት መጠን በሶስት እጅ ቀንሷል።

በማዕከላዊ ስታትስቲክስ መረጃ መሰረት ጠቅላላው የእርሻ ምርት በሰሜን ወሎ ከ1992—2001 ዓ.ም በእጥፍ አድጓል። በተመሳሳይ ጊዜ በፕሮጀክቱ ቀበሌዎች በመኸርና በበልግ ወቅቶች የነበረው የምርት እድገት ከጠቅላላው የሰሜን ወሎ የምርት እድገት ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ነበር። የመኸር ምርት እየጨመረ የመጣ ሲሆን በአንጻሩ ግን የበልግ ምርት ቀንሷል። ይህም የበልግ ወቅት ወደፊት እንደወትሮው የምርት ወቅት ላይሆን እንደሚችል ያመለክታል። በጥምር ፕሮግራሙ የመጨረሻ ምዕራፍ ወቅት የአካባቢው ነዋሪዎች የተሻሻሉ የእርሻ ዘዴዎችን መጠቀም ከመጀመራቸውም በላይ ሉትራን ባከናወናቸው ስራዎች ምክንያት ምርጥ ዘሮችንና ሌሎች የእርሻ ግብአቶችን የሚያገኙበት የተሻለ እድል ተፈጥሮላቸዋል። በብድግ ብድግ ናሙና (random sample) ውስጥ መካተት ከቻሉት የመስኖ እርሻ ተጠቃሚ የሆኑ ቤተሰቦች ሃያ አራት ብቻ ሲሆኑ ከነዚህም ውስጥ አስራ ሰባቱ ባሕላዊ መስኖ የሚሰሩ ናቸው። ስለዚህ የተገኘው የምርት እድገት በዘመናዊ መስኖ አጠቃቀም ምክንያት የመጣ ነው ለማለት አይቻልም ።

ይህን በመሰለ ህብረተሰብ ውስጥ የሚመጣን የእድገት መጠን ለመለካት የሚያገለግሉ ሶስቱ ጠቋሚዎች መሬት፣ ጉልበትና ከብቶች ሲሆኑ ከነዚህም ጋር የተያያዙ መለኪያዎች የሚያሳዩት እድገት መታየቱን ነው። በአሃዛዊ ጥናቱ የተካተቱ ቤተሰቦች አማካይ የመሬት ይዞታ ያለማቋረጥ እየጨመረ መጥቷል። በ1991 ዓ.ም በአራቱም ቀበሌዎች አማካይ የመሬት ይዞታ 0.59 ሄክታር ነበር። በ1996 ይህ ቁጥር ወደ 1.02 ሄክታር ያደገ ሲሆን በ2000 ዓ.ም ደግሞ ወደ 1.06 ሄክታር ከፍ ብሏል። ይህ አማካይ ጭማሪ የመጣው ተጨማሪ መሬት በመገኘቱ ሳይሆን ቀድሞ ጦሙን ያድር የነበረ መሬት ጥቅም ላይ እንዲውል በመደረጉ ነው። ለምሳሌ አራሽ ጉልበት ወይም ከብት የሌላቸው ቤተሰቦች መሬታቸውን ሲያከራዩ ጦሙን ያድር የነበረ መሬት ጥቅም ላይ ዋለ ማለት ነው። ጉልበትን በተመለከተ አንዱ መለኪያ በየቤተሰቡ ስንት ለስራ የደረሱ ሰዎች እንዳሉ ማየት ነው። አንድ ለስራ የደረሰ አዋቂ ወንድ ያለባቸው ቤተሰቦች ቁጥር መጠነኛ እድገት አሳይቷል - ከ65 በመቶ ወደ 69 በመቶ። በአንጻሩ ደግሞ ለስራ የደረሰ አዋቂ ወንድ የሌለባቸው ቤተሰቦች ቁጥር ቀንሷል። የጉልበት ሌላው መለኪያ የቤተሰቡ አባላት ጠቅላላ የጤና ሁኔታ ነው። ጥናቱ ከመካሄዱ በፊት በነበሩት አራት ሳምንታት በህመም ወይም በጉዳት ምክንያት ሊሰሩ ያልቻሉ የቤተሰብ አባላትን ቁጥር ስናይ በ1991 ዓ.ም 71 የነበረ ሲሆን በ1996 ቁጥሩ ወደ 16 ወርዶ በ2000 ዓ.ም ደግሞ ወደ 30 ከፍ ብሏል። ከብትን ያየን እንደሆነ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የእርሻ በሬዎች ያላቸው ቤተሰቦች ቁጥር በ1991 ዓ.ም 57 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2000 ዓ.ም ወደ 63 በመቶ አድጓል። በሬዎች የሌሏቸው ቤተሰቦች ቁጥር በአንጻሩ በተመሳሳይ መጠን በመቶኛ (ከ43 በመቶ ወደ 37 በመቶ) ቀንሷል። የእርሻ በሬን ጨምሮ የቤት እንስሳት ይዞታም ሲታይ ተመሳሳይ አዝማሚያ ታይቷል ። ይኸውም ምንም ከብት የሌላቸው ቤተሰቦች ቁጥር በግማሽ ሲቀንስ (ከ26 በመቶ ወደ 13 በመቶ) በአንጻሩ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የቤት እንስሳት ያሏቸው ቤተሰቦች ቁጥር ከ74 በመቶ ወደ 87 በመቶ አድጓል ።

እርሻ ነክ ያልሆኑም ሆነ ከእርሻ ቦታ ውጪ የሚከናወኑ ስራዎች በሰሜን ወሎ የገጠር ቀበሌዎች የሚጫወቱት ሚና እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። በአሃዛዊ ጥናቱ ከተካተቱት ቤተሰቦች ውስጥ ቆጠራው ከመካሄዱ በፊት ባሉት አራት ወራት ውስጥ እርሻ ነክ ባልሆኑ ስራዎች የተሳተፉ ግለሰቦች ቁጥር በ1991 ዓ.ም 15 የነበረ ሲሆን ይህ ቁጥር በ1996 ዓ.ም 33 ደርሶ ነበር። በ2000 ዓ.ም ደግሞ 23 ግለሰቦች ብቻ እርሻ ነክ ባልሆኑ ስራዎች ተሳትፈዋል። በገላጭ ጥናቱ ዘዴ ከአንዳንድ ቤተሰቦች ጋር በግልም ሆነ በቡድን የተደረጉ ውይይቶች እንደሚያመለክቱት እርሻ ነክ ያልሆኑም ሆነ ከእርሻ ቦታ ውጪ የሚከናወኑ ስራዎች በአጠቃላይ የጥምር ፕሮግራሙ በተንቀሳቀሰባቸው አካባቢዎች በሚኖረው ህዝብ ዘንድ እንደ ዋና የገቢ ምንጭ የሚወሰዱበት አጋጣሚ በጣም ውስን ነው። በጥምር ፕሮግራሙ የመጨረሻ ምዕራፍ ወቅት ወደ አረብ አገሮች የሚፈሰው የሰው ቁጥር በጉልህ የጨመረ ሲሆን በዚህም ሳቢያ ለአንዳንድ ቤተሰቦች ከውጭ የሚላከው ገንዘብ ዋና የገቢ ምንጭ ሆኖ ነበር።

እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ዋናው ጥያቄ የታዩት አዎንታዊ ለውጦች በጥምር ፕሮግራሙ ጣልቃ ገብነት የተገኙ ስለመሆናቸው እንዴት ማወቅ ይቻላል የሚለው ነው። በመጀመሪያዎቹ ሶስት የፕሮግራሙ ምዕራፎች ከተወሰኑ የመንግስት የልማት እንቅስቃሴዎች በስተቀር በአካባቢው የሚሰሩ ሌሎች የልማት ድርጅቶች አልነበሩም። በአራተኛው ምዕራፍ ግን ይህ ሁኔታ ተቀይሮ በዋናነት ምርታማ የሴፍቲኔት ፕሮግራም (Productive Safety Net Program) የሚሰጠውን የብድር አገልግሎት ጨምሮ ሌሎች የልማት ፕሮግራሞች በጥምር ፕሮግራሙ ቀበሌዎች ውስጥ መንቀሳቀስ ጀምረዋል።

በሶስተኛው ዙር አሃዛዊ ጥናት ከተሳተፉት 134 ቤተሰቦች ውስጥ ወደ 71 የሚሆኑት በሴፍቲኔት ፕሮግራም ውስጥ የታቀፉና የብድር አገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ነበሩ። በመጀመሪያዎቹ ሶስት ምዕራፎች ሉትራን የተገበረው የምግብ ለስራ ፕሮጀክት በርካታ ቤተሰቦች ለረጅም ጊዜ የምግብ እርዳታ እንዲያገኙ በማድረጉ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ በኩል ወሳኝ ሚና ተጫውቷል። በአራተኛው ምዕራፍ ግን ይህ በጥምር ፕሮግራሙ ይካሄድ የነበረዉ የምግብ ለስራ ፕሮጀክት ሴፍቲኔት በዘረጋው የምግብ እርዳታ ወይም የገንዘብ ክፍያ ፕሮጀክት ተተክቷል። በተጨማሪም በአራተኛው ምዕራፍ የግብርናና የገጠር ልማት ሚኒስቴር የግብርና ግብአቶችን በማቅረብ፣ ስልጠናዎችን በመስጠት፣ ወዘተ ንቁ ተሳትፎ አድርጓል። እንዲሁም ትምህርትን በተመለከተ እ.ኤ.አ የ2008 ሚሌኒየም ግቦችን ለማሳካት የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በማስፋፋት ረገድ መንግስት ሰፊ ስራ ሰርቷል። ያለእድሜ ጋብቻንና የሴት ልጅ ግርዛትን የመሳሰሉ ጎጂ ባህሎችን ለማስወገድም ቢሆን መንግስት የተጫወተው ሚና ቀላል አይደለም። ሆኖም እነዚህን ስራዎች ለማከናወን መንግስት የተጠቀመባቸው ዘዴዎች የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማዳበር ላይ ያተኮሩ ከመሆን ይልቅ በመጠኑም ቢሆን አስገዳጅ ነበሩ። ከ18 ዓመት በታች የሚደረግን ጋብቻ የሚከለክለው አዋጅ ተግባር ላይ የዋለበት መንገድ ለዚህ እንደምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል። በተጻራሪ የዴንማርክ ህፃናት አድን እና COLTA (Community Organization and Leadership Training for Action) ግብረ ሀይሎች ለበርካታ ዓመታት በአካባቢው ሲንቀሳቀሱ ህብረተሰቡ የህጻናት መብቶችን እንዲያከብር ለማድረግ የተጠቀሙበት ዘዴ በማስገደድ ሳይሆን በማስተማርና በእውቀት ላይ የተመሰረተ የአስተሳሰብና የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣ በማድረግ ነበር። በአጠቃላይ ሉትራን ያቋቋማቸው የCOLTA ግብረ ሀይሎች የጾታ እኩልነትን፣ የህጻናት መብትን፣ ጎጂ ባህሎችን፣ አመጋገብን፣ የቤተሰብ አስተዳደርንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች በሚመለከት የህብረተሰቡ ግንዛቤ እንዲዳብር ለማድረግ ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል። የፕሮግራሙ ጣልቃ ገብነት ያመጣው ለውጥ ጎልቶ እንዲታይ ያደረገው በከፊልም ቢሆን ሁለገብነቱ ነው። ይኸውም አንድ ፕሮጀክት የተቀረፀው የተለያዩ ዘርፎችን አዋህዶ በአንድ አካባቢ እንዲተገበር ተደርጎ ነው። ከላይ እንደተጠቀሰው ጥምር ፕሮግራሙ በተንቀሳቀሰባቸው አካባቢዎች በጤናው ዘርፍ ከ1991—2000 በነበረው ጊዜ መሻሻል ታይቷል። በተጨማሪም ህብረተሰቡ ምናልባትም የምግብ ለስራ ፕሮጀክቱ በፈጠረለት አጋጣሚ ምክንያት መሬቱን በተሻለ ሁኔታ ለማልማት የሚችልበት አቅም ፈጥሯል። በምግብ ለስራ ፕሮጀክቱ ውስጥ በመሳተፍ የተገኘው ተጨማሪ ገቢ ተጨማሪ መሬት ለማልማት አቅም የፈጠረ ሲሆን ይህ ደግሞ በተራው ለጠቅላላ ምርቱ ማደግ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

ከላይ የተጠቀሱት አዎንታዊ ለውጦች በጥምር ፕሮግራሙ እድሜ ከተከሰቱ አሉታዊ ሁነቶች አንጻር መታየት አለበት።

ለምሳሌ ከ1991—1993 የተካሄደው የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትና በ1992/3፣ በ1995/96 እና በ2000/2001 በአገሪቱ የነበረው የከፋ የምግብ እጥረት የሚጠቀሱ አሉታዊ ክስተቶች ናቸው፡፡ የጥምር ፕሮግራሙ መኖር የተከሰተው የምግብ እጥረት ቀውስ ሊያደርስ ይችል የነበረውን አሰቃቂ ጉዳት ቀንሶታል፡፡

በአጠቃላይ ጥምር ፕሮግራሙ ጣልቃ በገባባቸው ቀበሌዎች በሚኖረው ሕዝብ ሕይወት ላይ አዎንታዊ ለውጥ ማምጣቱ ጥርጥር የለውም፡፡ ሆኖም የህዝብ ብዛት በእርሻ መሬቱ ላይ እየፈጠረ ያለውን ጫናና ህዝቡ ከእርሻ ውጪ ባሉ ሙያዎች ጭምር እንዲሰማራና የገቢ ምንጭ አማራጮቹን እንዲያሰፋ በማድረግ ረገድ አመርቂ ስራ ባለመሰራቱ የምግብ እጥረት ችግር ዘላቂ በሆነ መልኩ ተፈቷል ለማለት አይቻልም፡፡ ሉትራን የንብ እርባታ ፕሮጀክቶችን በመተግበር፣ የብድርና ቁጠባ ማህበራትን በማቋቋም፣ ወዘተ ከእርሻ ውጭ የሆኑ ገቢ የሚያስገኙ ሙያዎችን ለህብረተሰቡ ለማስተዋወቅ የሞከረ ቢሆንም ሙከራው ስፋትና ጥልቀት ያልነበረው በመሆኑ ትርጉም ያለው ለውጥ ሊያመጣ አልቻለም፡፡ በአጠቃላይ ከእርሻ ውጪ በሆኑ ሙያዎች ላይ መሰማራትን በተመለከተ ህብረተሰቡ ውስጥ የአመለካከት ለውጥ ማምጣት አልቻለም፡፡ በተለይም በእድሜ ለገፋው አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ብቸኛው ስራና የገቢ ምንጭ ግብርና ነው፡፡ ነገር ግን መሬቱ በየጊዜው ለቤተሰቡ አባላት ሲከፋፈል መጠኑ እያነሰና ለምነቱንም እያጣ ስለሚሄድ ይህ አማራጭ ለብዙ ቤተሰቦች የሚያስኬድ አይደለም፡፡ ህዝቡ አሁንም የሚኖረው በግብርና ከሚያገኘው ምርት በተጨማሪ በሚሰጠው የምግብ እርዳታና በሴፍቲኔት የምግብ ለስራ ፕሮጀክት ውስጥ በመሳተፍ በሚያገኘው እህል ወይም ገንዘብ ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሰው ወደ አረብ ሐገሮች የመፍለስና ከውጪ ገንዘብ የመላክ ሁኔታ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመታየት ላይ ያለ አዲስ ክስተት ነው፡፡

ሌላው በጥምር ፕሮግራሙ አካባቢዎች የታየው አዲስ አዝማሚያ ህብረተሰቡ ለትምህርት የሰጠው ትኩረት ነው፡፡ በቆቦ ዙሪያ ከሚኖሩ አንዳንድ ቤተሰቦች ጋር በተደረገ አንድ የቡድን ውይይት ውስጥ የተሳተፉ አባላት እንደሚከተለው ገልጸውታል፤ "ልጆቻችን ይማሩ የምንለው መብታቸው ስለሆነ ብቻ ሳይሆን መማራቸው አስፈላጊ መሆኑን ስለምንገነዘብ ጭምር ነው፡፡ ካለው የመሬት ጥበት አንጻር ልጆቻችን ህይወታቸውን እዚህ ሊመሰርቱ አይችሉም፡፡" በእርግጥም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ሽፋን ጨምሯል፤ ትምህርታቸውን በአግባቡ የሚከታተሉ ህጻናት ቁጥርም ጨምሯል፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ ያለእድሜ ጋብቻንና የሴት ልጅ ግርዛትን የመሳሰሉ ሌሎች የህጻናት መብቶችን በተመለከተ ህብረተሰቡ የአመለካከት ለውጥ ማምጣት ብቻ ሳይሆን በተግባርም እያሳየ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ በአጠቃላይ የዛሬዎቹ የሰሜን ወሎ ህጻናት የተሻለ የትምህርት እድል ያገኙ፣ ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ የገበሬ ህይወት የተሻለ ተስፋ የሰነቁና የአዲስ ዘመን ተረካቢዎች ናቸው፡፡ ጥናቱ እንደሚያሳየው አብዛኞቹ የሰሜን ወሎ ሕጻናትና ህጻናትን ወክለው አስተያየት የሚሰጡ ወላጆች የሚመኙት የቢሮ ስራ ለመያዝ ነው፡፡ የእጅ ሙያ እንዲኖራቸው የሚመኙ በጣም ጥቂቶች ናቸው፡፡ ስለዚህ ትክክለኛውን አቅጣጫ ለማስያዝ በአንድ በኩል ህጻናቱ ስለእጅ ሙያ ያላቸውን አሉታዊ አመለካከት ለማስቀየር ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የተለያዩ ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎችንና ከእርሻ ውጪ የሆኑ ሙያዎችን በራሳቸው ተነሳሽነት የመፍጠር ፍላጎትና ክህሎት እንዲኖራቸው አስፈላጊውን ስልጠናና የዚሁም ማረጋገጫ የሚሰጥበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት፡፡ ከዚህ ጥናት የተገኘው አንዱና በጣም ጠቃሚው ትምህርት ስር የሰደዱ ባህላዊ ልማዶችን በተመለከተ በህብረተሰቡ ዘንድ ህጻን አዋቂ ሳይባል በአጭር ጊዜ ውስጥ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ነው፡፡

## 4. በፖሊሲ ላይ ያለው አንድምታ

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ፖሊሲ ማዕቀፍ በገጠርና በግብርና ላይ ያተኮረ ነው፡፡ አጠቃላይ የልማት ስትራተጂው ግብርና መር ኢንዱስትሪ ሆኖ ግብርናውና ኢንዱስትሪው ጎን ለጎን አብረው የሚያድጉበት አቅጣጫ ሳይሆን ግብርናው ቀድሞ ኢንዱስትሪውን እንዲመራ የታለመበት አካሄድ ነው፡፡

በ1997/98 ዓ.ም የተፋጠነና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማምጣትና ድህነትን ለማጥፋት የወጣው እቅድ (PASDEP) ሲጸድቅ እቅዱ ትኩረት የሰጠው የተለያዩ ከእርሻ ውጪ የሆኑ ሙያዎችን በማስፋፋት ቀስ በቀስ ከተማውንና ገጠሩን ለማገናኘት ነበር፡፡ ሆኖም ይህ የድህነት ቅነሳ ፖሊሲ እንዴት ወደተግባር እንደሚቀየር በዝርዝር የሚታወቅ ነገር አልነበረም፡፡ በተጨማሪም የድህነት ቅነሳ ስትራተጂው ቅድሚያ የሰጣቸው ጉዳዮች ክእርሻ ውጪ የሆኑ የሙያ ዘርፎችን ማስፋፋትና ከተማና ገጠርን የማገናኘት ስራ ሆኖ ሳለ የስትራቴጂው ፖሊሲ ማትሪክስ ግን ይህንን የሚያንጸባርቅ አይደለም፡፡ በፖሊሲ ማትሪክሱ እንደሚታየው አብዛኛው የሥራ እድል ይፈጠራል ተብሎ የታሰበው በሰብል ምርት፣ በአሳ ማጥመድና በከብት እርባታ ነው፡፡ ስትራቴጂው በእነዚህ ግብርና-ነክ በሆኑ ስራዎች ላይ ትኩረት ማድረጉ ከግብርና ውጪ ለሆኑ የስራ ዘርፎች ትኩረት መስጠቱን የሚያመለክት አይደለም፡፡

የድህነት ቅነሳ ፖሊሲው ያተኮረበት ሌላው ዓይነተኛ ጉዳይ ሴፍቲኔትንና ሌሎችንም ፕሮግራሞች ያካተተው የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ነው፡፡ ፖሊሲው የእርዳታ አሰጣጥ ስርዓቱን ከመሰረቱ በመቀየር በድንገተኛ አደጋ ለተጠቁ ብቻ እርዳታ ከመለገስ ይልቅ በተደጋጋሚ ለአደጋ የሚጋለጡ አካባቢዎችን አስቀድሞ በመለየት በነዚህ አካባቢዎች ለሚኖሩና የመስራት አቅም ላላቸው የምግብ ለስራ እድሎችን ሲሰጥ፤ የመስራት አቅም ለሌላቸው ደግሞ ነጻ እርዳታ ያበረክታል፡፡ ሆኖም የድህነት ቅነሳ ስትራተጂው ከሌሎች ፕሮግራሞች ጋር በቅንጅት የመስራት ችግር ያጋጠመው በመሆኑ በሴፍቲኔት ታቅፈው ከቆዩ የህብረተሰቡ አባላት ውስጥ ራሳቸውን እየቻሉ የሚወጡትን የመለየቱን ስራ በብቃት ለማከናወን ተስኖታል፡፡ የህዝብ ብዛት በእርሻ መሬቱ ላይ የሚያሳድረው ጫና መጨመር፣ የኢንዱስትሪ ልማቱ ውሱንነት፣ ህዝቡ ከክልል ወደ ክልል የሚያደርገው ዝውውር የተገደበ መሆኑና በመሬት ይዞታ ላይ ሙሉ ዋስትና አለመኖሩ የምግብ ዋስትና ፕሮግራሙ ጥረቶች ዘላቂነት ያለው ለውጥ እንዳያመጡ አድርገውታል፡፡ መንግስት በ1996 ዓ.ም የጀመረውና በ1998 ዓ.ም አጠናክሮ የገፋበት የመሬት ምዝገባና የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የመስጠት ሂደት አርሶ አደሩ በመሬቱ ላይ የተሻለ የባለቤትነት ዋስትና እንዲኖረው በማድረግ በኩል አንድ እርምጃ ወደፊት መራመዱን ያሣያል፡፡ ነገር ግን አሁንም ጎልተው የሚታዩት እውነታዎች መሬት በመንግስት ቁጥጥር ስር መሆኑ፣ በመሬት ላይ የሚደረጉ ግብይቶች የተገደቡ መሆናቸውና የመሬት ባለቤትነት መብት ገጠር ውስጥ ኗሪ ከመሆን ጋር መያያዙ ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ የሚደረግ ፍልሰት አሁንም የተገደበ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በተወሰነ መሬት ላይ ጫና እንዲኖር ከማድረጉም በላይ የገጠር አካባቢዎች ወደ ከተማነት ለማደግ የሚያደርጉትን ሂደት በጣም አዝጋሚ ያደርገዋል፡፡ የምግብ ዋስትና ፕሮግራሙ ለተጠቃሚ ቤተሰቦች ገቢ በሚያስገኙ የስራ መስኮች ላይ መሰማራት የሚያስችሏቸው የሙያ ስልጠናና የመሳሰሉ አገልግሎቶች አይሰጥም፡፡ በሰሜን ወሎ የተደረገው ይህ ጥናት እንደሚያሳየው የምግብ ዋስትና ፕሮግራሙ ለተጠቃሚዎቹ የሚሰጠው የብድር ገንዘብ በአብዛኛው የሚውለው ለከብት እርባታና እንደ እርሻ በሬ የመሳሰሉ ለግብርና ስራ የሚያገለግሉ ቁሳቁስ መግዣ እንጂ ከግብርና ውጪ የሆኑ ሙያዎችን ለመፍጠርና ለማሳደግ አይደለም፡፡ በቅርቡ የተደረገ አንድ ግምገማ[*] በምግብ ዋስትና ፕሮግራምና በሌሎችም ተጓዳኝ ፕሮግራሞች ውስጥ ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎች የሚያካብቷቸው የግብርና መሳሪያዎች/ቁሳቁስ መጠን እያደገ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ሆኖም የተጠቃሚዎቹ የንብረት መጠን እድገት ተጠቃሚ ያልሆኑ ሰዎች ላይ ከታየው እድገት የፈጠነ አይደለም፡፡ ምናልባትም የምግብ ዋስትና ፕሮግራሙ አሁን ባለበት ምዕራፍ (ከ 2003 ዓ.ም እስከ 2007 ዓ.ም) ንብረት የማሳደግን ስራ በቤተሰብ ደረጃ ወርዶ ለመስራት ስላቀደ ግቡን ሊመታ ይችል ይሆናል፡፡ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች ግን የንብረት ማሳደጉ ስራ የተካሄደው በማህበረሰብ ደረጃ

[*] Gilligan, Daniel, O. John Hoddinott and Alemayehu Seyoum Taffesse. 2008. The Impact of Ethiopia's Productive Safety Net Programme and its Linkages. International Food Policy Research Institute (IFPRI) Discussion Paper 00839.

ነበር። በአዲሱ ምዕራፍ የምግብ ዋስትና ፕሮግራሙ የመንግስትን የቤተሰብ ንብረት ግምባታ ፕሮግራም (HABP) ለማገዝ በሚያሥችል መንገድ ዳብሯል። ይህ የመንግስት ፕሮግራም የሚያተኩረው የምግብ እጥረት ላለባቸው ቤተሰቦች የገንዘብ አገልግሎትና ሙያዊ ድጋፍ በመስጠት፣ የገቢ ምንጮችን በማበራከት፣ ምርታማነትን በማሻሻልና የማምረቻ መሳሪያዎች ባለቤትነትን በማሳደግ በአጠቃላይ የምርት ስርአቱን ወደላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ነው። ነገር ግን ይህ የመንግስት ፕሮግራም በርካታ ችግሮች ታይተውበታል። ከነዚህም ውስጥ የፋይናንስ ምርቶችን በብቃት ለመለየት አለመቻሉ፣ የሚሰጠው ብድር ለግብርና ስራዎች እንጂ ለሌሎች ሙያዎች ትኩረት ያልሰጠ መሆኑ፣ የብድር አገልግሎቱ በሙያው በተካኑ አገልግሎት ሰጭዎች አለመከናዎኑና በአጠቃላይ የአፈጻጸም ድክመት ያለበት መሆኑ ሊጠቀሱ ይችላሉ። ከዚህም በተጨማሪ ይህ ንብረት የማከማቸት ስራ በስፋት ከተካሄደ የራሱ አሉታዊ ገጽታዎች ሊኖሩት ይችላሉ። ለምሳሌ የህብረተሰቡ የከብቶች ባለቤትነት ሲጨምር መሬቱ ከልክ በላይ ለሆነ ግጦሽ ሊጋለጥ ይችላል።

## 5. ማጠቃለያና የፖሊሲ ሀሳቦች

የድህነት ቅነሳ ፖሊሲው የገጠሩን አካባቢ ወደ ከተማነት መቀየርንና ከግብርና ውጪ የሆኑ ሙያዎችን መስፋፋት የሚደግፍ ሆኖ ሳለ፣ የምግብ ዋስትና ፕሮግራሙም ያነጣጠረው ለረጅም ጊዜ የድርቅ ተጠቂ የሆኑ አካባቢዎችን መሆኑ ይበል የሚባል ሆኖ፣ በገሀድ የሚታየው እውነታ ግን አገሪቷ አሁንም ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ የግብርና ምርት ልትላቀቅ አለመቻሏ ነው። የአፍሪቃ ቀንድ አካባቢ በአለም ውስጥ በአየር ጠባይ ለውጥ በከፍተኛ ደረጃ ከሚጠቁ አካባቢዎች አንዱ ነው። በተለይም በአሁኑ ወቅት በመከሰት ላይ ያለው የከባቢ አየር ለውጥ ይህንን አካባቢ ለከፋ አደጋ አጋልጦታል። ስለሆነም በዚህ በከባቢ አየር ለውጥ ክፉኛ በተጋለጠ አካባቢ የኢትዮጵያን የኤኮኖሚ ልማት በከፍተኛ ደረጃ ተለዋዋጭ በሆነ የዝናብ ውሃ ላይ ተንጠልጥሎ እንዲቀጥል ማድረግና ምርታማነቱ ዝቅተኛ በሆነ የግብርና ዘዴ እየተጠቀሙ መቀጠል ትክክለኛ አማራጭ ሊሆን አይችልም። የአማራ ክልልን በተመለከተ ዝናብ ጠብቀውና ከፍተኛ ጉልበት ተጠቅመው የዕለት ጉርሳቸውን ለማግኘት ያልተሳካላቸውን አርሶ አደሮች ከግብርና ውጭ ወደሆኑ ሙያዎች እንዲሰማሩ ማገዝ ያስፈልጋል። ለአማራ ክልል ይበጃሉ ተብለው የታሰቡ የመፍትሄ ሀሳቦች የሚከተሉት ናቸው።

### *ሀ. ባሕላዊ ተጽዕኖን ለማስወገድ የማነቃቂያ ስራ መሰራት*

የተለያዩ የስራ መስኮች እንዳይስፋፉና የተሻለ የምግብ ዋስትና እንዳይኖር ከሚያደርጉ መሰረታዊ ችግሮች አንዱ ለአንዳንድ የእጅ ሙያዎችና ከእርሻ ውጪ ለሆኑ ስራዎች ህብረተሰቡ ያለው አሉታዊ አመለካከት ነው። ከልምድ እንደታየው ህብረተሰቡ የብድር አገልግሎት አገኘ ማለት በራሱ ከእርሻ ውጪ በሆኑ ሙያዎች ይሰማራል ማለት አይደለም። የብድር ገንዘቡ አብዛኛውን ጊዜ የሚውለው ባሕላዊ ለሆኑ የሙያ ዓይነቶች፣ ለግብርና፣ ለከብት እርባታ፣ ወዘተ. ነው። ስለዚህ ህብረተሰቡ ከነዚህ ውጪ ከሆኑ ሙያዎች ጋር እንዲተዋወቅ የማድረግ ስራ መስራት ወሳኝ ነው። የጥምር ፕሮግራሙ ጥናት እንዳሳየው ያለዕድሜ ጋብቻንና የሴት ልጅ ግርዛትን በመሳሰሉ ባሕላዊ ተግባራት ላይ ህብረተሰቡ ያለውን አመለካከት ለመቀየር የተሰራው የግንዛቤ ማዳበር ስራ ውጤት አስገኝቷል። የእጅ ሙያንና ንግድን በተመለከተ የሰፈነው አሉታዊ አመለካከት ደግሞ በገጠር ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በመንግስት ደረጃ ሳይቀር የሚንጸባረቅ ነው። አንዳንድ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም የተለያዩ ከእርሻ ውጪ የሆኑ የሙያ ዘርፎችን በህብረተሰቡ ዘንድ ለማስተዋወቅ የሚያደርጉት ጥረት በዋናነት በዚሁ ባሕላዊ ተጽዕኖ ሳቢያ አመርቂ ውጤት ሊያስገኝ አልቻለም። ስለዚህ የእነዚህ ሙያዎች መስፋፋት ምን ያህል አስፈላጊና ጠቃሚ እንደሆነ ህብረተሰቡም ሆነ መንግስት እንዲረዱ ለማድረግ በዚህ ጉዳይ የተሰማሩ አካላት ሰፊ የማነቃቂያና የግንዛቤ ማዳበሪያ ስራ መስራት ይኖርባቸዋል፡

### *ለ. የብድር አገልግሎት ከሙያዊ ስልጠና ጋር መጣመር*

በአማራ ክልል ብድርና ቁጠባ ተቋም አማካኝነት በአለፉት ጥቂት ዓመታት በክልሉ በርካታ ሰዎች የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል። ሆኖም ለጥቃቅንና አነስተኛ የንግድና የሙያ ዘርፎች እንዲውል የታቀደው የብድር ገንዘብ አንዳንድ ጊዜ የእለት ጉርስን ለመሸፈንና ለሌሎችም ችግሮች ማቃለያ የዋለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በድህነት ቅነሳ ፕሮግራሙ በኩል የሚገኘውም ብድር በአብዛኛው የሚውለው ለከብት እርባታና ለግብርና መሳሪያ/ቁሳቁስ መግዣ ነው። ከዚህ ለመረዳት የሚቻለው የብድር ገንዘብ መስጠት በራሱ የተለያዩ ሙያዎች እንዲስፋፉ ሊያደርግ አለመቻሉን ነው። በዚህም ምክንያት ነው የብድር ገንዘብ አቅርቦቱ ከሙያ ስልጠና ጋር መያያዙ አስፈላጊ የሚሆነው። ስለሆነም ከድህነት ቅነሳ ፕሮግራሙ ጋር በተጉዋዳኝነት የሚሰሩት ሌሎች የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞች የሚሰጡት የብድር አገልግሎት ከሙያ ስልጠና ጋር የተያያዘ እንዲሆን ከሙያ ማሠልጠኛ ተቋማት ጋር በመተባበር ሊሰሩ የሚችሉበትን መንገድ ማመቻቸት ይኖርባቸዋል። የሙያ ትምህርት ዓይነቶች ምርጫ ጥናትን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት።

### *ሐ. ግንኙነትን ማጠናከር*

በቆላውና በወይናደጋው ወይም በደጋው ኗሪዎች፣ በደሀውና በመለስተኛ ደሀው ቤተሰቦች፣ እንዲሁም በከተማውና በገጠሩ ኗሪዎች መካከል የመተባበር መንፈስ መኖር አለበት። ለምሳሌ በከተሞች አካባቢ የሚኖሩ የተሻለ ሀብት ያላቸው ቤተሰቦች ባሕላዊ በሆነ የመስኖ ስራ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፤ በቆላማው አካባቢ የሚኖሩ ቤተሰቦች ደግሞ በአንፃራዊ መልኩ ሰፋ ያለ መሬት ያላቸው ናቸው። እንዲሁም ከእርሻ ውጪ በሆኑ ሙያዎች ለመሰማራት የተሻለ ዕድል አላቸው። በከተማ አካባቢ የሚኖሩ መለስተኛ ድሆችን የኢኮኖሚ አቅም መገንባት ገጠር ውስጥ ያሉ ድሆች ተቀጥረው ሊሰሩ የሚያስችላቸውን አጋጣሚ ሊፈጥር ይችላል። ለምሳሌ መሬት የሌለው የገጠሩ ደሀ ከተማ ባለው መለስተኛ ደሀ መሬት ላይ አራሽ ወይም ከብት ጠባቂ ሆኖ ሊቀጠር ይችላል፤ ለእኩል ምርት ክፍያ ወይም የዘር እህል ሊያከራየው ይችላል፤ ወይም ከእርሻ ውጪ በሆኑ ስራዎች ላይ ሊሰማራ ይችላል። እንዲሁም በወይናደጋና በደጋ አካባቢ የሚኖሩ መሬት አልባ ድሆች ስራ ፍለጋ ሰፋፊ መሬት ወዳለባቸው ቆላማ ስፍራች ይፈልሳሉ። በአጠቃላይ የከተሞች ልማት ለገጠሩ የሚሰጠው ጥቅም አለ። ስለዚህ ማንኛውም በልማት ስራ ላይ የተሰማራ ኃይል እነዚህን ትስስሮች ማጤንና ማጠናከር አለበት። ለምሳሌ በከተማ ልማት ላይ የተሰማራ ኃይል የገጠሩን ህዝብም ለማገዝ የሚረዱ እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርበታል።

*ፐርኒል ሶረንሰን እና ሰሎሜ በቀለ*

**ምንጭ**:- Sørensen, Pernille and Selome Bekele. 2009. ‘***NICE CHILDREN DON’T EAT A LOT OF FOOD’***. Strained Livelihoods and the Role of Aid in North Wollo, Ethiopia. Addis Ababa: FSS.

**አድራሻ:- ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ፣ ፖ.ሳ.ቁ 25864 ኮድ 1000 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**
**❄ ስልክ 011-629 78 88/91 ❄ ፋክስ 011-629 78 89**
**❄ ኢሜይል: fss@ethionet.et ❄ ድረ-ገፅ www.fssethiopia.org.et**